# የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ
# የ2011 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2011 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል።

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፣ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው። እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል። ኦዲታችን ፦

- በሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል።

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይጨምራል።

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል።

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው ሪፖርቶች መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም በኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው። ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው።

የሚከተሉት የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ኤጀንሲ የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል::

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የገዘውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

**ለኦዲት አስተያየቱ መሠረት የሆኑት ጉዳዮች፣**

የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቁ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፣

**ወጪ፤**

1. የታብሌት ኮምፒዩተሮችን ግዥ ለመፈጸም የዋጋ ማወዳደሪያ ያቀረቡ ድርጅቶች ኤጀንሲው ከሚፈልገው ተቀራራቢ የጥራት ደረጃዎች ላይ ዋጋ እንዲሰጡ ሳይደረግ በብር 184,000.00 ግዥ ተፈጽሞ ተገኝቷል::
2. ለመሰረታዊ የጋዜጠኝነት ስልጠና ከተከፈለ የውሎ አበል ብር 207,140.00 ውስጥ ስልጠና እንዲሰጥ የተያዘው ፕሮግራም ለ10 ቀናት/16/4/11-25/4/11 በመሆኑ ብር 126,760.00 መከፈል ሲገባው ለ20 ቀናት ብር 207,140.00 ተከፍሎ በመገኘቱ ብር 80,380.00 በብልጫ ወጪ ሆኖ ተገኝቷል::

**ተሰብሳቢ ሂሳብ፤**

3. በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 42,673.01 ተገኝቷል::

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 3 ከተገለፁት ሁኔታዎች በስተቀር በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሣብ ሪፖርቶች በበጀት ዓመቱ እስከ ሰኔ 30 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የተሰበሰበውን ገቢ የተፈፀመውን ወጪና የበጀት አጠቃቀሙን በአጥጋቢ ሁኔታ ያሳያሉ::

**ትኩረት የሚሻ ጉዳይ፤**

4. ለስልክ አገልግሎት የተፈጸመ ክፍያ ብር 209,520.13 በሂሳብ መደብ 2241108/6258/ መመዝገብ ሲገባው በአገልግሎት ክፍያ 2241106/6256/ የሂሣብ መደብ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡
5. የመደበኛ በጀት ብር 18,870,561.25፤

   የካፒታል በጀት ብር 32,686,372.14

በድምሩ ብር 51,556,933.39 ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት መገኘቱ ታውቋል፡፡

**ሌሎች ጉዳዮች፤**

**ንብረት**

6. በኤጀንሲው ውስጥ ለሚገኙት ቋሚ እቃዎች የመለያ ቁጥር ተሚልቶ አለመሰጠቱን፤
7. በንብረት ክፍል ቢን ካርድ እና ስቶክ ካርድ በጥቅም ላይ ቢውሉም የመኪና መለዋወጫ ዕቃዎች አይነታቸውን በሚገልፅ ሁኔታ ያልተደራጁ መሆኑን፤
8. አገልግሎት መስጠት የሚችሉና የማይችሉ በርካታ ቴሌቪዥኖች፤ የቴሌ ፕሪንተር መሳሪያዎች፤ የጥቁር እና ነጭ ማተሚያዎች እና ሌሎች ዕቃዎች በንብረት ክፍል ተከማችተው ለብልሽት በመዳረግ ላይ የሚገኙ መሆኑን፤
9. የሰሌዳ ቁጥሩ 4-03194-ኢት የሆነ ላንድ ክሩዘር እና የሰሌዳ ቁጥር 30-054 ሾርት ቤዝ ተሽከርካሪዎች በብልሽት ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ ቆመው ምንም ዓይነት እርምጃ ያልተወሰደባቸው መሆኑ፤
10. አንድ ቶዮታ ፒክ አፕ መኪና ለረጅም ጊዜ በብልሽት ምክንያት ከአገልግሎት ውጭ ሆኖ የቆመ መሆኑን፤
11. ኤጀንሲው የሚገለገልባቸው ስድስት መኪናዎች የባለቤትነት ማረጋገጫ መታወቂያቸው በሌላ ተቋም ስም መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

ከሠላምታ ጋር

---------------------

ትዕግስት ረታ
የንግድና አስተዳደር መ/ቤቶች
ኦዲት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር